Centers for Disease Control and Prevention
CDC 24/7: Saving Lives, Protecting People™

# ወላጆች ስለ ኩፍኝ በሽታ ሊያቋቸው የሚገቡ 4 ዋና ዋና ነገሮች

ኩፍኝ በጣም ተላላፊ እና ከባድ ሊሆን የሚችል በሽታ ነው። አንድ ያልተከተበ ልጅ ከውጪ ሃገር በሚጓዝበት ጊዜ ወይም በU.S. ውስጥ እንኳን ኩፍኝ ሊይዘው ይችላል። ሁለት የMMR ክትባት ዶዞች ልጅዎን ከኩፍኝ በሽታ ለመከላከል የተሻለ ጥበቃ ያቀርባሉ።

እርስዎ እንደ ወላጅ ስለ ኩፍኝ ማወቅ ያለብዎት ምን እንደሆነ እያሰቡ ይሆናል። CDC እንደ እርስዎ ላሉ ወላጆች ስለ ኩፍኝ በሽታ በጣም ወሳኝ የሆኑትን እውነታዎች ዝርዝር አዘጋጅቷል።



## 1. የኩፍኝ በሽታ በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል።


አንዳንድ ሰዎች ኩፍኝ ትንሽ ሽፍታ እና በጥቂት ቀናት ውስጥ የሚጠፋ ትኩሳት እንደሆነ ያስባሉ ነገር ግን **ኩፍኝ በተለይም ከ5 በታች በሆኑ በትናንሽ ህጻናት ላይ** ከባድ የጤና ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል። ልጅዎ ሊያጋጥመው የሚችለውን የበሽታ ምልክቶች ክብደት አስቀድሞ መናገር የሚቻልበት መንገድ የለም።

- በU.S. ውስጥ በኩፍኝ ከተያዙ ከ5 ሰዎች ውስጥ 1 ሆስፒታል ይገባል
- ኩፍኝ ካለባቸው ከ1,000 ሰዎች ውስጥ 1 ሰው የአንጎል እብጠት የሚያጋጥመው ሲሆን ይህም ወደ አንጎል ጉዳት ሊያመራ ይችላል
- ኩፍኝ ከያዛቸው 1,000 ሰዎች ምንም እንኳን የተሻለ እንክብካቤም ቢደረግላቸውም ከ1 እስከ 3 የሚሆኑት ሰዎች ይሞታሉ።

የተወሰኑት በጣም የተለመዱ የኩፍኝ ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ከፍተኛ ትኩሳት (ከ104 ° F በላይ ከፍ ሊል ይችላል)፣
- ሳል፣
- ንፍጥ (coryza)፣
- ቀይ፣ በእንባ የተሞሉ አይኖች (ልባሰ አይን)፣ እና
- ሽፍታ (የበሽታ ምልክቶች ከጀመሩ ከ3-5 ቀናት በኋላ)።

bit.ly/MeaslesSymptoms



## 2. ኩፍኝ በጣም ተላላፊ በሽታ ነው።

የኩፍኝ በሽታ አንድ በበሽታ የተያዘ ሰው ሲያስል ወይም ሲያስነጥስ በአየር ላይ ይዛመታል። በጣም ተላላፊ በሽታ በመሆኑ አንድ ሰው ከያዘው በዙሪያው ካሉት 10 ሰዎች 9 የሚሆኑት ጥበቃ ካልተደረገላቸው በበሽታው ይያዛሉ። ልጅዎ የኩፍኝ በሽታ ያለበት ሰው በነበረበት ክፍል ውስጥ በመገኘቱ ብቻ፣ ያ ሰው ከሄደ ከሁለት ሰዐት በኋላ ቢሆንም እንኳን የኩፍኝ በሽታ ሊይዘው ይችላል። የታመመ ሰው **በሽታው እንዳለበት ከማወቁ/ቋ በፊት ቢሆንም እንኳን ወደ ሌሎች ሰዎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ—** የኩፍኝ ሽፍታ ከመከሰቱ ከአራት ቀናት በፊት እና እዚያ በኋላ እስከ አራት ቀናት ድረስ።

bit.ly/MeaslesTransmission

Centers for Disease Control and Prevention
CDC 24/7: Saving Lives, Protecting People™



## 3. ልጅዎ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ሆኖም በኩፍኝ በሽታ ሊያዝ ይችላል።

በጣም ውጤታማ ለሆነው የክትባት ፕሮግራም ምስጋና ይድረስና ኩፍኝ ከአሜሪካ መጥፋቱ በ 2000 ታውጇል። ጠፍቷል ማለት በሽታው ከእንግዲህ በዚህ አገር ውስጥ በቋሚነት አይኖርም ማለት ነው። ይሁን እንጂ፣ የኩፍኝ በሽታ በብዙ የአለም ክፍሎች ውስጥ አሁንም የተለመደ ነው።

ምንም እንኳን ቤተሰብዎ በአለም አቀፍ ደረጃ ባይጓዝም፣ በማህበረሰብዎ ውስጥ በማንኛውም ቦታ ከኩፍኝ ጋር ሊገናኙ ይችላሉ። በየአመቱ፣ የኩፍኝ በሽታ በሌሎች አገሮች በሚኖሩበት ጊዜ ኩፍኝ በያዛቸው ባልተከተቡ ተጓዦች (በአብዛኛዎቹ አሜሪካዊያን እና አንዳንድ ጊዜ የውጭ አገር ጎብኝዎች) አማካኝነት ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ይመጣል። ከኩፍኝ በሽታ ያልተጠበቀ ማንኛውም ሰው ተጋላጭ ነው።

bit.ly/PlanForTravel



## 4. በአስተማማኝ እና ውጤታማ በሆነ ክትባት ልጅዎን ከኩፍኝ በሽታ የመጥተበቅ አቅም አለዎት።

የኩፍኝ በሽታን ለመከላከል የተሻለ የሆነው መከላከያ የኩፍኝ-ጆሮ ደግፍ-ሩቤላ (MMR) ክትባት ነው። የ MMR ክትባት ከሁሉም የኩፍኝ በሽታ ዝርያዎች ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ጥበቃ ይሰጣል።

ለተሻለ ጥበቃ ልጅዎ ሁለት ዶዝ የMMR ክትባት ያስፈልገዋል፡-

- የመጀመሪያው ዶዝ ከ 12 እስከ 15 ወር እድሜ ላይ ሲሆነው
- ሁለተኛው ዶዝ ከ 4 እስከ 6 አመት እድሜ ሲሆነው

ዎ ወደ ውጪ ሃገር የሚጓዝ ከሆነ፣ የክትባት ምክረሃሳቦች ከዚህ ትንሽ ይለያሉ፡-

- የልጅዎ እድሜ ከ6 እስከ 11 ወር ከሆነ፣ እሱ ወይም እሷ ከመሄዳቸው በፊት 1 ዶዝ የ MMR ክትባት ሊወስዱ ይገባል።
- የልጅዎ እድሜ 12 ወር ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፣ እሱ ወይም እሷ ከመሄዳቸው በፊት 2 ዶዝ የ MMR ክትባት (ቢያንስ በ28 ቀናት ልዩነት) መውሰድ ያስፈልገዋል።

ሌላኛው ክትባት፣ ከ4 በሽታዎች የሚከላከለው የኩፍኝ-ጆሮ ደግፍ-ሩቤላ-ቫሪሴላ (MMRV) ክትባት ሲሆን እድሜያቸው ከ 12 ወራት እስከ 12 አመት ለሆነ ህጻናትም ተዘጋጅቷል።

bit.ly/MealesVax